የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
A.A. KALITI CUSTOMES BRANCH OFFICE
የውስጥ መፃፃፊያ
INTER OFFICE MEMORANDUM

ቁጥር ም.ሥ.አ/086/04
ቀን 20/07/2005

ለ ዕቅድ አፈፃፀምና ክትትል የሥራ ሂደት
ለ ጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት
ለ ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት
ለ መንግሥት የተሠጡ መብቶች የሥራ ሂደት
ለ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
ለ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
ለ ተመላሽ ስርዓትና የገቢ ሂሳብ አስተዳደር የሥራ ሂደት
ለ መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
ለ ልዩነት ሕጣሪ 1 እና 2 ቡድኖች
ለ ዋጋ ትመና ቡድን
ለ ሪከርድና ማህደር ቡድን

ከ ም/ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት

ከዋና መ/ቤት ከኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በደብዳቤ ቁጥር 1.5/156/6 በቀን 18/07/2005 በተፃፈ ደብዳቤ ተሻሽሎ የፀደቀውን ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን ተሻሽሎ የፀደቀውን መመሪያ ቁጥር 4/2005ን 1 ጥራዝ ለተገቢው አፈፃፀም የተላከ መሆኑን እየገለፅን በስራችሁ ላሉ ቡድኖችና ፈፃሚ አካከሎች እንዲያውቁት እንዲደረግና በዚሁ መሠረት ተፈፃሚ እንዲሆን አሳስባለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

- ለ ዋና ሥራ አስኪያጅ
- ለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ /ኦፕሬሽን/

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1.5/156 16
Ref. No
ቀን 18 መጋቢት 2005
Date

ለቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በደብዳቤ ቁጥር አሰ4/16/1 ቀን 6/07/05 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተሻሽሎ የፀደቀውን ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቅዱ ተሽከርካሪዎችን አይነትና ብዛት ለመወሰን ተሻሽሎ የፀደቀውን መመሪያ ልከልናል፡፡

ስለሆነም ለተገቢው አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2005ን 1 ጥራዝ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
- ለኦፐሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥራዎች ዘርፍ
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ቡድን

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች

# በጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ

## ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ

## መመሪያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Agency

መጋቢት 4 ቀን 2005 ዓ.ም

# ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ከአዲሱ የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 እና ይህንኑ ደንብ ለማስፈጸም ከወጣው የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለለ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 ጋር አጣጥሞ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 እና ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 14 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ - ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2005 ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2
## ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ፡-

1) ‹‹ተሽከርካሪ›› የሚለው ቃል የደረቅ፣ የፍሳሽ/የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪናን ወይም ለተለየ አገልግሎት ተብለው የሚዘጋጁ ተመሳሳይ መኪኖችን፤ ፒክ-አፕን፣ ማናቸውም ዓይነት ስቴሽን ዋገንን፣ ከሕዝብ መንገድ ውጭ አገልግሎት የሚሰጥ ልዩ መኪናን (ቶም ካርን) ፣ አውቶቡስን፣ ሚኒባስን፣ ሸፍን የዕቃ ማጓጓዣ መኪናን (ዴሊቨሪ ቫንን) እና ሞተር ብስክሌትን የሚያካትት ነው፡፡

2) ‹‹አውቶቡስ›› ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ቢያንስ 30 መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3) ‹‹ሚኒባስ›› ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ10 ያላነሰ እና ከ15 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

4) ‹‹ፒክአፕ›› ማለት 2WD ወይም 4WD የሆነ፣ የሲሊንደሩ ብዛት በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከሆነ ከ4 ያለበለጠ፤በሌሎች አካባቢዎች ከሆነ ከ6 ያልበለጠ እና የመጫን አቅሙ ከ500 ኪ.ግ. እስከ 1500 ኪ.ግ. የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

5) ‹‹ዴሊቨሪ ቫን›› ማለት የመጫን አቅሙ ከ3000 ኪ.ግ. እስከ 5000 ኪ.ግ. የሆነ ሸፍን የጭነት ተሽከርካሪ ነው፡፡

6) ‹‹የጭነት መኪና›› ማለት ተሳቢውን ጨምሮ የመጫን አቅሙ ከ5000 ኪ.ግ. በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

7) ‹‹ለተለየ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ›› ማለት የሥራ መስኩ ልዩ ባህርይ የሚጠይቃቸውና ለመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የማይውሉ ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡

8) ‹‹ሞተር ብስክሌት›› ማለት የሞተር አቅሙ ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪ ነው፡፡

9) ‹‹ሆቴል››፣ ‹‹ሎጅ››፣ ‹‹ሬስቶራንት››፣ እና ‹‹ሞቴል ›› በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

10)‹‹ሪዞርት ሆቴል›› ማለት ለመዝናናት፣ የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ፣ ወዘተ. በሚያስችል መልኩ ከከተማ ወጣ ብሎ በመዝናኛ ሥፍራዎች የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው፡፡

11)‹‹የኢንዱስትሪ ቀጣና›› በኢንቨስትመንት ዓዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

12) ‹‹ዓዋጅ›› ማለት የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቊጥር 769/2004 ነው፡፡

13) "ደንብ" ማለት ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቊጥር 270/2005 ነው፡፡

14) በኢንቨስትመንት ዓዋጁና ደንቡ ለተለያዩ ቃላትና ሐረጋት የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው የኢንቨስትመንት መስኮችና የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

### አንቀጽ 3

### የተሽከርካሪ ማበረታቻ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች

በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጠው በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት፣ የኮከብ ደረጃ

ባላቸው ሆቴሎች (የሪሶርት ሆቴሎችን ጨምሮ)፣ ሞቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና ሎጆች፣ በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት፣ በአስጎብኝነት ሥራ እና በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ የሥራ መስኮች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ለሚያቋቁሙ ወይም ነባር ድርጅታቸውን ለሚያስፋፉ ባለሀብቶች ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4
## ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በዚህ መመሪያ በሠንጠረዥ አንድ ከተመለከቱት የሥራ መስኮች በአንዱ ቢያንስ 10 ሚሊዮን ብር ካፒታል ለፕሮጀክቱ የሚያውል ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀዱለት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተመለከተው በሥራ መስክ እና በሚቋቋምበት የልማት አካባቢ ይሆናል፡፡

2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከቱት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Agency

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የአስተዳደር አካባቢዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | | በሌሎች አካባቢዎች | | |
| | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ፒክ አፕ መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| የእንፋሎት ማመንጫዎችን ማምረት | | | | | | |
| 13.2. የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ምስማርን ሳይጨምር ሌሎች የብረታ ብረት ውጤቶችን (የእጅ መሣሪያ፣ ቁሳቁስ እና የመሳሰሉትን) ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 14. የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ<br>14.1. የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |
| 14.2. ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን ማምረት<br>14.3. የመገናኛ መሣሪያዎችን ማምረት<br>14.4. የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ (ቴሌቪዥን፣ዲ.ቪ.ዲ፣ ሬድዮ እና የመሳሰሉ) ዕቃዎችን ማምረት<br>14.5. የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 14.6. የሕክምና መሣሪያዎችን (ኢራዲየሽን፣ ኤሌክትሮ-ሜዲካል ወይም ኤሌክትሮ -ቴራፒቲክ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 14.7. የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ዕቃዎችን ማምረት<br>14.8. መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አይፈቀድም |

5) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ለኢንቨስትመንቱ ያዋለው የካፒታል መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የካፒታል መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 5

## ለግብርና ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በዚህ መመሪያ በሠንጠረዥ ሁለት ከተመለከቱት የሥራ መስኮች ቢያንስ በአንዱ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀዱለት ተሽከርካሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተገለፀው መሠረት በሚያለማው የመሬት ስፋት፣ በሚኖረው የእንስሳት ብዛት፣ የቀፎ ብዛት ፣ የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ባዋለው የመሬት ስፋት ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቱ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት፣

   ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ወይም ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

   ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት ፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠው ማስረጃ፣ እና

   ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

መ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግገርውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ 'መ' የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለሀብት ከፒክ-አፕ፣ የጭነት መኪና እና ሞተር ብስክሌት በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ያለማው የመሬት ስፋት ወይም ያለው የእንስሳት ብዛት ወይም የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ያዋለው የመሬት ሥፋት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው መጠን የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

5) ለእርሻ ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሥንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

## አንቀጽ 6

### ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ በመክፈል ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

   ሀ/ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም የሚመለከተው ሌላ የመንግሥት አካል ለየደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሣሪያዎች በዋጋ 25% ያሀሉን ከውጭ አገር ስለመግዛቱ ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice) ወይም ሌላ የዋጋ ግምት ማረጋገጫ ሠነድ ፣ ወይም

   ለ/ መሣሪያዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

<u>ሠንጠረዥ ሦስት</u>

## ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ሥራዎች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በተቋራጭነት ደረጃ

| ተራ ቁጥር | የኮንስትራክሽን ዘርፍ | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሦስት | ደረጃ አራት | ደረጃ አምስት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | 1.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | 1.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| | 1.3. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| | 1.4. የውኃ መርጫ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| 2. | የሕንፃ ሥራ ተቋራጭነት | | | - | - | - |
| | 2.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | 2.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| | 2.3. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 3. | የመንገድ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | 3.1. ፒክ አፕ | 2 | 1 | 1 | 1 | - |
| | 3.2. የውኃ መያዣ የተገጠመለት መኪና | 1 | 1 | - | - | - |
| | 3.3. የውኃ መርጫ የተገጠመለት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 4. | ልዩ ሥራ ተቋራጭነት (ለኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ብቻ) | | | | | |
| | 4.1. ፒክ አፕ | 1 | 1 | - | - | - |
| | 4.2. የጭነት መኪና | - | - | - | - | - |
| 5. | <u>የውኃ ሥራ ኮንስትራክሽን ተቋራጭነት</u> | | | | | |
| | 5.1. የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1 የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |
| | 5.2. ሌላ የውኃ ሥራ ኮንስትራክሽን ተቋራጭነት | 2 | 1 | - | - | - |
| 6. | የመሠረት ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ መቆፈሪያ/መሰርሰሪያ መሣሪያ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1 የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |
| 7. | የማዕድን ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 1 ፒክ አፕ ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1የጭነት መኪና፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |

## አንቀጽ 7

### የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) የኮከብ ደረጃ ባለው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንት ወይም የሎጅ አገልግሎት የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚያወጣውን የደረጃ መሥፈርት መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ አራትን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ተሽከርካሪዎችን ከውጭ ማስገባት ይችላል፡፡

### ሠንጠረዥ አራት

#### የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኮከብ ደረጃ

| ተ.ቁ. | የኮከብ ደረጃ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | 1 ወይም 2 | 1 ፒክ አፕ |
| 2. | 3 ወይም በላይ | 2 ፒክ አፕ |

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ በባለሀብት ሲጠየቅ፦

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ማስረጃ፣ እና

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የሕንፃው ግንባታ፣ መሠረተ-ልማት እና መጋዘን የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማስረጃ

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም እንደ አግባቡ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 8

## ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

በኢንቨስትመንት ቦርድ በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 መሠረት ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ዴሊቨሪ ቫን ከውጭ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡ ሆኖም የሚያስገባው ዴሊቨሪ ቫን ብዛት ከ3 አይበልጥም፡፡

## አንቀጽ 9

## ለአስጎብኝነት አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት 3 አዳዲስ ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪዎችን በአንድ ዓመት ውስጥ በሁለት ጊዜ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስጎብኝነት የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት አንድ አውቶቡስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ተሽከርካሪዎቹን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡-

   ሀ/ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ያወጣውን መሥፈርት በማሟላት አግባብ ካለው አካል የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ አውጥቶ/አግኝቶ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ወይም ወደ ኢንቨስትመንት መስኩ የሚሠማራ መሆን ይኖርበታል፡፡

   ለ/ ተሽከርካሪዎቹ አዳዲስ ስለመሆናቸው ከተፈበረኩበት/ባቸው ፋብሪካ/ዎች ወይም ከአቅራቢዎች ማስረጃ ማቅረብ እና ተሽከርካሪዎቹን ለማስጎብኘት ሥራ ብቻ እንደሚያውላቸው በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ፊት ቀርቦ ግዴታ መግባት ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ በቅድሚያ፣

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ/ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ አገር ስለመገዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Track-way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

ሐ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከአገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢ ውል ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር፣

መ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የሕንፃ ግንባታ፣ መሠረተ-ልማት፣ መጋዘን እና መንገድ የመሳሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማስረጃ፣ እና

ሠ/ ለፕሮጀክቱ በቋሚነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ስም ዝርዝር የያዘ ቢያንስ የሦስት ወር የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Pay-roll) እና ለመንግሥት የደመወዝ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅድው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

## ሠንጠረዥ ስድስት

ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በቋሚ ሠራተኛ ብዛት

| ቋሚ የሠራተኛ ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ25 - 50 | 2 ሚኒባስ ወይም 1 አውቶቡስ |
| ከ50 በላይ | 3 ሚኒባስ ወይም 2 አውቶቡስ |

እንዲገባለት ጥያቄውን ባቀረበበት ወቅት ምርቱን ወደ ውጭ እየላከ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል::

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 13

### በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ/ስለሚመረቱ ተሽከርካሪዎች

ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብት ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ/ማምረቻ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ሲገዛ ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ የተሽከርካሪው ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተሠልቶ ይቀነስለታል::

### አንቀጽ 14

### የማስፋፊያ/የማሻሻያ ኢንቨስትመንቶች

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት ኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ እና በኢንቨስትመንት ዓዋጁ መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ/ያሻሻለ ባለሀብት ለማስፋፊያ/ለማሻሻያ ፕሮጀክቱ በአንቀጽ 4፣ 5፣ 10፣ 11 እና እንደአግባቡ በአንቀጽ 12 ከተመለከቱት የተሽከርካሪ ዓይነቶች አንዳንድ ተሽከርካሪ በነዚሁ አንቀጾች በተደነገገው መሠረት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል::

### አንቀጽ 15

### መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Agency

## አንቀጽ 16

### የተሻረ መመሪያ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎች

1) ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ተሽሯል፡፡

2) በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት የኢንቨስትመንት መስክ ከገቢ ግብርና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የሚሰጥባቸው የሥራ መስኮችና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚገቡ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ዓይነት ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 አንቀፅ 5 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

3) ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 17

### የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈቀዱ የተሽከርካሪ ማበረታቻዎችን በሚመለከት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

ይህ መመሪያ ከ መጋቢት.4.ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል

**አዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

የኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ